በዚህ አግባብ ለደረጃው የተቀመጠውን አካዳሚክ ኮርስ ስለማጠናቀቃቸው ስልጠናውን ከሚወስዱበት ዩኒቨርሲቲ ማስረጃ ካቀረቡ የማስተማር ሙያ ስልጠና ባያጠናቅቁም እስከ 2016ዓ.ም ሐምሌ ድረስ ግዜውን ጠብቆ ለአንድ ጊዜ ብቻ ትይዩ የደረጃ እድገት ያገኛሉ።

ሆኖም የማስተማር ሙያ /PGDT/ ስልጠና ተመዝኝቶላቸው ስልጠናውን ለመውሰድ ፍቃደኛ ያልሆኑ መምህራን ለደረጃው የተቀመጠውን ደረጃ እድገት ተጠቃሚ የማይሆኑ ሲሆን ቀድሞ በነበሩበት (ድፕሎማ) የትምህርት ዝግጅትና ለዚሁ በተፈቀደው የትምህርት እርከን ተመድበው ለደረጃው የሚገባቸውን ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኙ ይደረጋል።

2.3 የትምህርት መረጃ ጋር በተያየዘ የትምህርት ደረጃቸውን ለማሻሻል በትግራይ ክልል በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ስልጠና ሲከታተሉ የነበሩና በጊዜያዊነት በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው በየትምህርት መስኩ /አካዳሚክ/ ኮርሶችን ያጠናቀቁ፣ እንደዚሁም የማስተማር ሙያ (PGDT) ሥልጣናን ጀምረው ቢያጠናቅቁም ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉ መምህራን ዋናው የውጤት ሰነዳቸው እስከሚገኝ ድረስ ከከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሚሰጣቸውን/የተሰጣቸውን ጊዜያዊ መረጃ ሲያቀርቡ ከላይ በቀረቡ ማብራሪያዎች አግባብ የደረጃ ዕድገቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ነገር ግን ሁኔታዎች ወደ መደበኛ አሰራር ሲመለስ የትምህርት ማስረጃቸውን ተከታትለው ለማቅረብ ማመልከቻ ጽፈው በማህደራቸው ውስጥ ሊያኖሩ ይገባል። መምህራኑ ዋናውን ሰነድ ሲያቀርቡ ከውጤታቸው ጋር ተያይዞ ችግር ከተገኘ የተፈቀደው የደረጃ እድገት የሚሰረዝ ከመሆኑም በላይ በዲሲፕሊን የሚያስጠይቃቸው መሆኑን በፍርማቸው ማረጋገጥ ይኖርበቸዋል።

2.4 በግላቸው የትምህርት ደረጃቸውን ከድፕሎማ ወደ መጀመሪያ ድግሪ ያሻሻሉ በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን ለደረጃ እድገት ለመወዳደር ከሚያበቁ መሠረታዊ መስፈርቶች በተጨማሪ ቀጥለው የተመላከቱ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ ከትምህርት ደረጃ ጋር የተያያዘ የደመወዝ ማሻሻያ ይደረግላቸዋል።

